መልእክት አምስት

## ቤተ ክርስቲያን የእውነት ዓምድ እና መሠረት
## እና ብዙዎች የተካተቱበት የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ የመሆኗን
## እውነት ማጽናት እና ለዚህ እውነት መመስከር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ጢሞ. 3፡15-16፤ 2፡4፤ 2 ጢሞ. 2፡15፤ ዮሐ. 18፡37

**I. ቤተ ክርስቲያን እውነትን ደግፋ የምትይዝ ዓምድ እና አጽንታ የምትይዝ መሠረት ናት—1 ጢሞ. 3፡15፦**

ሀ. ጌታ ቤተ ክርስቲያኑ እርሱ እውነት ስለመሆኑ ትመሰክር ዘንድ እንደ እውነት እንድታውቀው ይፈልጋል—ዮሐ. 14፡6፤ 18፡37፤ 1 ዮሐ. 1፡6፤ 5፡20፦

ለ. በ 1ኛ ጢሞቴዎስ *እውነት* የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ስለተገለጡት እውነተኛ ነገሮች ነው፣ እነዚህም በዋነኛነት የእግዚአብሔር አካል መልበስ የሆነው ክርስቶስ እና የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ናቸው—2፡4፤ ቆላ. 2፡9፣ 19።

ሐ. እውነት ቤተ ክርስቲያንን እንደ የክርስቶስ አካል፣ እንደ የእግዚአብሔር ቤት እና እንደ የእግዚአብሔር መንግሥት ለማፍራት ክርስቶስ እንደ አካል መልበሱ፣ ማዕከሉ እና መገለጡ የሆነው ሦስታንዱ አምላክ ነው—ቁ. 9፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡16፤ 1 ጢሞ. 3፡15፣ ዮሐ. 3፡3፣ 5።

መ. ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን እንደ እውነታ ትሸከማለች፤ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ እና ክርስቶስ ብቻ እውነታ መሆኑን ለመላው አጽናፍ-ዓለም ትመሰክራለች—1፡14፣ 17፤ 14፡6።

ሠ. እውነትን እንደምትሸከም ዓምድ እና ዓምዱን አጽንታ እንደምትይዝ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምሥጢር የመሆኑን እና ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ምሥጢር የመሆኗን እውነታ፣ እውነት ትመሰክራለች—ቆላ. 2፡2፤ ኤፌ. 3፡4።

ረ. የምንገነባው የቤተ ክርስቲያን አይነት የሚወሰነው በምናስተምረው የትምህርት ዓይነት ላይ ነው፤ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍራት፣ ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት እና ቤተ ክርስቲያን መኖር እንድትቀጥል ለመርዳት ሕያው የሆነው እውነት አንገብጋቢ አስፈላጊነት አለ—1 ጢሞ. 3፡15።

ሰ. የግድ ማሟላት የሚያስፈልገን ታላቁ ፍላጎት ቅዱሳንን ወደ እውነት ማምጣት ነው፤ ሁሉም ቅዱሳን በመለኮታዊው መገለጥ መሰልጠን አለባቸው—2፡4።

**II. ሁሉም ቅዱሳን እውነትን አጽንተው ሊይዙ ያስፈልጋል—3፡9፣ 15፤ 2 ጢሞ. 2፡15፦**

ሀ. እውነትን ደግፋ የምትይዘው ዓምድ እና አጽንታ የምትይዘው መሠረት ቅዱሳንን ሁሉ ጨምሮ መላዋ ቤተ ክርስቲያን ናት፤ የቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ ብልት እውነትን አጽንቶ የሚይዝ የዓምዱ እና የመሠረቱ ክፍል ነው—1 ጢሞ. 3፡15።

ለ. ቤተ ክርስቲያን የእውነት ዓምድ እና መሠረት መሆኗ የሚያመለክተው የቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ ብልት እውነትን ማወቅ እንዳለበት ነው፤ ስለዚህ፣ እውነትን ለመማር መወሰን አለብን—2፡4፦

1. ቤተ ክርስቲያን፣ እያንዳንዱን አማኝ ጨምሮ፣ እውነትን አጽንታ መያዝ አለባት—3፡9።
2. ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ እንድትሆን እያንዳንዱ ወንድም እና እኅት እውነትን በመማር፣ እውነትን በመለማመድ እና እውነቱን መናገር በመቻል እውነትን አጽንተው መያዝ አለባቸው—2፡4።
3. እውነትን በየዕለት የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በተግባር ከተለማመድነው፣ እውነትን አጽንቶ በመያዝ የተወሰነ ኃላፊነት መሸከም የምንችል እንሆናለን—2 ዮሐ. 4፤ 3 ዮሐ. 3-4፣ 8።

**III. ቤተ ክርስቲያን ብዙዎች የተካተቱበት የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ የመሆኗን እውነት አጽንተን መያዝ እና ለዚህ እውነት መመስከር ያስፈልገናል—1 ጢሞ. 3፡15-16፦**

ሀ. የእግዚአብሔር መገለጥ በመጀመሪያ በክርስቶስ እንደ አንድ ግለሰብ በሥጋ የሆነ መገለጥ ነበር—ቁ. 16፤ ቆላ. 2፡9፤ ዮሐ. 1፡1፣ 4፦

1. አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋ ለበሰ አይልም፤ እግዚአብሔር በሥጋ እንደተገለጠ ይገልጣል—1 ጢሞ. 3፡15-16፦

   ሀ. እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠው እንደ ወልድ ብቻ ሳይሆን እንደ መላው እግዚአብሔር—አብ፣ ወልድ እና መንፈስ—ነው።

ለ. እግዚአብሔር ወልድ ብቻ ሳይሆን መላው እግዚአብሔር ሥጋ ለበሰ፤ በመሆኑም፣ ክርስቶስ በተሠግዎው መላው እግዚአብሔር በሥጋ መገለጡ ነበር፡-

(1) በተሠግዎው በነበረው አገልግሎቱ፣ ክርስቶስ የማይወሰነውን አምላክ ወደ ውስኑ ሰው ውስጥ አመጣው፤ በክርስቶስ የማይወሰነው አምላክ እና ውስኑ ሰው አንድ ሆኑ—ዮሐ. 8፡58፤ 7፡6፤ 12፡24።

(2) በተሠግዎ በኩል መለኮታዊው መካተት—እግዚአብሔር በመለኮታዊ ሥላሴው አንዱ በሌላው ውስጥ መኖሩ እና እንደ አንድ አብሮ መሥራቱ—ወደ ስብዕና ውስጥ መጣ፤ ስለዚህም ክርስቶስ የሦስታንዱ አምላክ ሦስት ክፍል ካለው ሰው ጋር መካተት ነው—14፡10-11።

2. በክርስቶስ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል—ቆላ. 2፡9፡-

ሀ. *የመለኮት ሙላት ሁሉ* የሚያመለክተው መላውን መለኮት፣ ሙሉውን አምላክ ነው።

ለ. መለኮት አብን፣ ወልድን እና መንፈስን ስለያዘ፣ የመለኮት ሙላት የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ ሙላት መሆን አለበት።

ሐ. የመለኮት ሙላት ሁሉ በክርስቶስ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል ማለት ሦስታንዱ አምላክ በእርሱ አካል ለብሷል ማለት ነው—ዮሐ. 14፡10።

መ. እንደ የመለኮት ሙላት አካል መልበስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ሳይሆን መላው እግዚአብሔርም ጭምር ነው።

ለ. አንደኛ ጢሞቴዎስ 3፡15-16 ክርስቶስ እንደ ራስ ብቻውን የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ እንዳልሆነ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንም እንደ የክርስቶስ አካል እና የእግዚአብሔር ቤት የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ እንደሆነች ያመለክታል—እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር፡-

1. በቁጥር 16 *እግዚአብሔርን መምሰል* የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር ያለ አክብሮትን ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር የመኖሩ፣ ማለትም እግዚአብሔር እንደ ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ለመገለጥ መኖሩን ነው፡-

ሀ. ክርስቶስ እና ቤተ ክርስቲያን ሁለቱም እግዚአብሔርን በሥጋ የሚገልጡ እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ናቸው።

ለ. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ተገቢ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ኑሮ ነው—1 ቆሮ. 1፡6፤ 14፡24-25።

2. እግዚአብሔር የሚገለጠው እንደ ተለቀችው ብዙዎች የተካተቱባት በሥጋ መገለጥ በቤተ ክርስቲያን—በእግዚአብሔር ቤት እና በክርስቶስ አካል—ነው—ኤፌ. 2፡19፤ 1፡22-23፡-

ሀ. የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ የጀመረው ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ነው—ዮሐ. 14፡9።

ለ. የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ፣ የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ መጨመር፣ መተለቅ እና መባዛት በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ይቀጥላል—1 ጢሞ. 3፡15-16።

ሐ. እንዲህ ያለችዋ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ እግዚአብሔርን በሥጋ የመግለጡ—ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር መገለጥ በቤተ ክርስቲያን የመኖሩ—መቀጠል ትሆናለች።

3. ታላቅ የሆነው እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ለእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ ብዙዎች የተካተቱበት አምላክ-ሰው ለማፍራት ሰው በሕይወት እና በባሕሪ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ ነው—ሮሜ 8፡3፤ 1፡3-4፤ ኤፌ. 4፡24።

*© 2021 Living Stream Ministry*